**" የመዳን መንገድ፤ ወደቦታዬ የመመለስ ብቸኛ ምርጫ "**

አትብላ የተባልኩትን ባለመታዘዝ በላው ።ሁሉን ነገር ተሰጥቶኝ፤ምድርንም እንድገዛ ስልጣን ሰጥቶኝ ፤ከራሱ ጋ እንድኖር፣ፈቅዶ ወዶና አቅርቦኝ፤ እራሱ መግቦኝ፤

እኔ ግን ለሰይጣን መንገድ ከፈትኩ ፤በእግዚአብሔር ላይ ዋሻው፤ አታክልቱን "ተንከባከበኝ" ብሎኝ እያለ፤ጭራሽ እግዚአብሔር 'አትንካ' ብሎኛል ብዬ ለሰይጣን እግዚአብሔርን አለመውደዴን በውሸተ አረጋገጥኩ፤

ይህንን ክፍተት ተጠቅሞ ሰይጣንም ሰበኸኝ "እንደ እግዚአብሔር ትሆናላችሁ " አለኝ፤እግዚአብሔር ላይ ያመፀው ልቤ #እግዚአብሔር ለመሆን ወደደ ፤እንደ እርሱ መፍጠር ፤እንደ እርሱ የሁሉ በላይ ፤እንደ እርሱ ሁሉን አዋቂ ለመሆን ወደደ፤

በቃ፤መታዘዘንና አለመታዘዘን ለማየት የተቀመጠችውን በለስ በላው ፤እግዚአብሔርን ካድኩት፤አልበላም ማለት እየቻልኩ፤ በራሰው ፈቃድ በላው፤ አሥ በመብላቴ እንደ 'እግዚአብሔር ሆንኩኝii ' አሥ ከእግዚአብሔር ያልሆነውን ክፉውን እውቀት አወኩ፤መልካም ለማድረግ ብፈልግ እንኳ መልካሙን ለማድረግ አቂም የሚያሳጣኝ ኃጢአት በእኔ ውስጥ ሆነ ፤ አሁን ምን ይሻላል ?

የጽድቅ አይኖቼ ተዘጉ ፤ባለመታዘዝ የተከፈተው የዐመጻ ዓይኖች ተከፈቱ፤ተመለከትኩ ፤ ቸርነት እንደ ራቀኝ አወኩ፤ከእርሱ ጋ ውበት የሆነብን ሁሉ ያለ እርሱ ማፈሪያ ሆነ፤በፀጋው ከእግዚአብሔር ጋ ተስማምተን ነበር የሚንኖረው ፤አሁን ግን አይደለም ከእግዚአብሔር ከመለኮቱ ጋር ይቅርና እርስ በእርስ እንኳ ያለ ፀጋው ለሰከንድ መተያየት አልቻልንም ፤እርስ በእርስ ለመተያየት ኑቀጠል ለመበጠስ ደረስን፤ቅጠሉንም ለራሳችን ሰፋን ፤ልካችን ባይሆንም ልካችን ነው ብለን ተቀበልን፤ግን ከእግዚአብሔር እንዴት እንደበቅ ? በሚመስል ነገር ራሳችንን ደበቁን ግን እግዚአብሔር ይታለላል በዚህ አሁን? ከዚህ ጭንቀት( ራቁትነት) ሳልወጣ ሌላ ችግር መጣልን።የሰፋነው ቅጠል፤አይደለም ከእግዚአብሔር ለመደበቅ ለራሳችን እንኳን ፀሐይ ስመጣ አይሸፍነንም።እሺ ምን ይሻላል ? የት ልደበቅ ? እንደት ልውጣ ከዚህ ማአት?

ፈራው ፤ከቅጠል የሚሻል የቅጠሉን ምንጭ ዛፍን ብጠቀም ብዬ አሰብኩ ፤ዛፍን አየሁ ፤እጅግ በጣም ትልቅ ነው ፤ኃጢአተን ለመደበቅ ሞከርኩ፤ዛፍ እኮ ነው ብያንስ ገላያን ይደብቃል ፤ግን ህልናየንስ የት ልደብቁ? ዛፉ ግን አይደለም ለህልናየ ለገላየ እንኳን አልሆነም።ንፋስ ስመጣ ይወዛወዛል፤እርቃነን እንደሆንኩ ያሳውቅብኛል።ወይ መርበትበት "ለራሱ እንኳ በንፋስ የሚገዋለለውን ዛፍ ለመደበቅ ማሰቤ "፤ምን ይሻላል? በምን ልደበቅ ?ከእግዚአብሔር እንደራኩ ታውቆኛል? ከእርሱ ጋ እያለሁ ያለኝን

ሰላሜን ሳጣ ይታወቀኛል ፤ አሁንስ ምርጫዬ ምንድነው ?

የአምላክ ድምጽ ይመላለሳል ፤እንደዚህ የሚጠራኝ እርሱ እንደሆነ ታውቆኛል፤በህልናየም በቃልም ይጮሃል ።ድምጹ ቁጣ አለሁ፣ድምጹ ልጄ ለምን ይላል? ፣ድምጹ ፍለጋውን ያሳውቃል ፤እንዳወቀብኝ አወኩ።ወዴት ነህ አለኝ ? ምን ልበል ? ተመለስ ማለቱ ታውቆኛል፤ንስሐ ግባ ማለቱ ታውቆኛል።አሁንም ጨክኖ የካደው ልቤ ለንስሐ መች እሺ ይላል ።ሌላ አማራጭ ፈለኩ ከዚህ ማ'ጥ ለመውጣት ።ቅጠል ሞከርኩ አልሆነልኝም ፤በአታክልቶቸ ላይ ለመደበቅ ሞከርኩኝ አልተሳካልኝም ፤ዓይኔን ቀና ብዬ ሳየሁ ከጎኔ መደበቂያ አገኘሁ.....

እኔ በእጄ ቀጥፌ አልወሰድኩም ፤ይህንን ሁሉ ደፍራ እሷ ባትወስድ አልበላም "እሷናት ያሳሳተችን" እላለሁ ብዬ አሰብኩ።ራሴን ለመደበቅ ጥፋቱን ላለማመን የማላደርገው ነገር የለም።ጭራሽ በእግዚአብሔር ላይ ካላሳበብኩ ብዬ አሰብኩ "አተን ባትሰጠኝ ይህ ሁሉ ይደርስብኝ ነበር" አንተም ጌታ ሆይ ተጠያቂ ነህ? መጀመሪያ ለምን ሰጠሄኝ ብዬ ለመክሰስም፤ለማሳበብም፤ጣሪኩ፤ስሰጠኝ ማመስገኔን ረሳው ፤ "አጥንቱ፣ ስጋዬ "ማለቱን ረሳው፤ራሴን ለማስመለጥ ስል ከጎኔ የነበረችውን አጥንቱን ካድኩ፤ ጌታ ግን ሔዋንንም ጠየቃጥ ....

ለምን አደረግሽ አለ?።እርሷም እንደ አዳም አሳበበች ፤ጌታ ሆይ "እኔን አትጠይቀኝ አንተ የፈጠርከውን እባቡን ጠይቅ" ለማለት ወደደች።ጌታን ለመክሰስ ፈለኩኝ፤መጀመሪያ ለምን እባብን ፈጠርክ ለማለትም ወደድኩ ፤ቆፍጠን ብዬ እኔ "አይደሉም እባብ ነው" አልኩ ።ለሁለት ተደምረናል በእግዚአብሔር ላይ #ሽምጥጠናል።ወዬ አለማፈር...

አሁን ተስፋዬ ተሟጠጠ ።መደበቂም ማሳበብም አላዋጣኝም ።ጌታን ማረኝ እንኳን አላልኩም ፤ ምህረት ፈለኩኝ ግን የጌታዬ ቁጣ ነድዷል ። #ግን_ስለነ_ማን_ይቀርብልኛል ?

እግዚአብሔርም ፦ይህን ካደረክ ምን እንደምመጣ ወስነው ነውና ያለው ።በዚህ ቃል መሠረት ፈረደኝ።እኔም የእጄን ነው ብዬ ዝም አልኩ። የሞከርኩት ሁሉም አላዋጣኝም፤ከዚህ ውጭ ሌላ የጎጢአት መደበቂያ መንገድ አላውቅም ፤እኔም ፈጽሞ አድነኝ ብዬ አልለመንኩም፤

ግን እግዚአብሔር ሁሉም ድንቅ ነው።ሞትን ትሞታለህ ብሎ እንኳ ተስፋ ሰጠኝ።እኔን ያዋረደኝን እባብ የሚበቀል እንዳለ አሳወቀኝ።ጌታ ፈጽሞ እንዳልገደለኝ ተረዳሁ ።ግን እሱን ለምን ብለ፦ግን ይጠይቃል ? እሱ ሉዓላዊ ነው።ለላ ሰው እኮ መፍጠር ይችላል ።ሌላ የተሻለ ሰው እኮ መሥራት ይችላል ።ግን ለእኔ ብሎ አሁንም እኔ

ሳልጠይቅ፤ሳልለምን፤በራሱ ፈቃድ፤ እንድሁ እኔን አላጠፋም ብሎ አንድ ንፁህ በግ አረደልኝ።

እንደተራቆትኩ በእርቃን ነኝ ፤ዛፍ ስሪ ነኝ ፤ቅጠል ሰፊቻለሁ፤በማሳበብ ላይ ነኝ።ግን ይህ ሁሉ ነፃ አያወጣም ብሎ በግ አረደ ለዚያውም ንፁህ በግ አረደልኝ።አበላኝ ፤አለበሰኝ፤አሁንም እርቃነን ስሸፍን፤አሁንም ራበን ስያስጠግብ፤አሁንም ሲችለኝ በደሌን፤ስሸከመኝ ባዶነቱን፤ዝም ብሎ መውደዱ ገርሞኛል ።እየፈጠረ ደክሞ የለፋውን ፍጥረት ለእኔ ብሎ ያለ ምህረት ስያጠፋ አረደልኝ፤ለእኔ ግን በፍርዱ ምህረቱን ፤በጭቀናውን ፍቅሩን፤ባለቀልኝ ነገር ላይ ተስፋ ሰጠኝ፤

እሺ ወደ ቦታዬ ለመመለስ አሁን ምን ላድርግ ? እሱ የሰጠኝን ተስፋ አምኜ ልቀበል ወይንስ ሌላ የአካራጭ መንገድ ልፈልግ?ግን አቋራጭ መንገድ በራሱ አለው?የለም። መጀመሪያውኑ የጠፋሁት የራሴን መንገድ በመፈለግ፤በማድረግ ነው።እሱን፦ በጉን ብቻ ተስፋ አደርጋለሁ ።ስለዚህም ምክንያት ሚስቴ ሔዋን ናት።አዎ ተስፋ አለኝ ።በንፁህ በግ ደም ብቻ ወደ ቦታዬ እመለሳለሁ ፤አልራቆጥትም።እንግዲህ የሚለብሰው የሚበላው የሚደበቀው የሚጠለለው ፦በበጉ በእርሱ በክርስቶስ ብቻና ብቻ እንደሆነ ተረድቻለሁ ።

የተኛውም ፍጡር ወደቦታየ እንደማይመልሰኝ ተረዳሁ ፤በጉን እበላለሁ እጠጣለሁ እለብሳለሁ እሱም፦ኢየሱስ ብቻ ነው። መዳን እግዚአብሔር የሰጠኝን በግ በእምነት በመቀበል በመብላት በመጠጣት በመልበስ እንደሚገኝ ተረድቻለሁ ።ይህ ቀጥታ ወደ ቦታየ የሚመልሰኝ ፍጹም የእውነት መንገድ ነው።ጆሮ ያለው ይስማ ።

እድሉ ዮሐንስ ጋምሳ
ተባረኩ